# ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ አመራረት
# ትርፍ በትርፍ ወደ ሆነ ልማት!

ከ ኃይለማርያም ወንድሙ 7/6/12

ቀደምት መንግስታት የተስተካከለ የልማት ፖሊሲ ባለመንደፍ እንዳውም ዕድገትን ከማቀላጠፍ ይልቅ የማደናቀፍ ሚና የነበራቸው የተሳሳቱ ፖሊሲዎችን ቀይሰው በስራ ላይ በማዋላቸው ኢኮኖሚያችንን ለመሰረታዊ መዋቅራዊ ችግር አጋልጠውት ቆይተዋል፡፡ በየዓመቱ በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ወገኖቻችን የምግብ ዕርዳታ ለመጠየቅ የተገደድነው በምግብ እህል እንኳን ራሳችን መቻል ስላቃተን እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡

ለዘመናት በቆየ መዋቅራዊ ችግር የተተበተበው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ እንኳን ለሌሎች ክፍለ ኢኮኖሚዎች ዕድገት መፋጠን መነሻ ሊሆን ቀርቶ የህዝባችንን የምግብ ፍላጎት ለማርካት የሚያስችል ምርት የሚታፈስበት መሆን አልቻለም ነበር፡፡

መንግስት ያወጣው ግብርናንና ገጠርን ማዕከል ያደረገው የልማት ስትራቴጂ የሚያስገኘው ጠቀሜታ 85 በመቶ የሚሆነውን የገጠር ህዝብ ከድህነት ማላቀቅ እና ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ብቻ አይደለም፣ የከተማውን ህዝብም ከድህነት በማላቀቅና ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግም ረገድ እጅግ ተመራጭ የልማት አቅጣጫ ነው፡፡

ግብርና በከፍተኛ ደረጃ በሚያድግበትና ብዙ ምርት በሚመረትበት ወቅት በተትረፈረፈ ምርት ምክንያት የግብርና ምርቶች ዋጋ መቀነሱ አይቀርም፡፡ የከተማው ህዝብ ከዚህ ተጠቃሚ ሲሆን፣ አምራቹ የምርቱ ዋጋ ቢወርድበትም የግብርና ምርቱን በብዛትና በጅምላ ስለሚሸጥ ከፍተኛ ገቢ ያገኛል፡፡

ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረገው የልማት ስትራቴጂ የግብርና ምርቶች ዋጋ ቀንሶ የከተማው ሸማች እንዲጠቀም፣ የንግድና እንዱስትሪ ዕድገት ተፋጥኖ የከተማው ህዝብ የስራ ዕድገት እንዲያገኝ ከማድረግ ባሻገር የሚካሄደው የኢንዱስትሪ ዕድገት የሰውን ጉልበት በሰፊው የመጠቀም ባህሪ ባለው የኢንዱስትሪ ዓይነት ላይ ያተኮረ እንዲሆን በማድረግ የሚፈጠረው የስራ ዕድል በሌላ አማራጭ ሊኖር ከሚችለው ሁሉ እጅግ የሰፋ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

ተከታታይና ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማስመዝገብ መንግስት የቀረጸው ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገው የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ በገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት በጥራትና በብዛት ለማምረት፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና የኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን እየረዳ ነው፡፡

በዚህም አርሶ አደሩ ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ የአመራረት ዘይቤ ተላቆ ወደ ገበያ መር የአመራረት ዘይቤ ተሸጋግሯል፡፡ ከዚህም በላይ በሀገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ በርካታ አርሶ አደሮች ድህነትን አሸንፈው በመቶ ሺዎች እና በሚሊዮኖች የሚቆጠር ካፒታል ባለቤቶች ለመሆን ችለዋል፡፡

የግብርና ልማት ዕድገታችን ከዓለም ገበያ ጋር የተሳሰረ በመሆኑ ዕድገቱ ወደኋላ ወደ ማይመለስበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ይህ በመሆኑም የግብርና ዕድገታችን ባለፉት ሰባት ዓመታት በየዓመቱ በአማካይ የ10 በመቶ ዕድገት በማስመዝገቡ አጠቃላይ የአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በአማካይ ከ10 በመቶ በላይ ከፍ እንዲል የመሪነቱን ሚና ተጫውቷል፡፡

መንግስት የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን ምርታማነት ለማሳደግ ምርጥ ዘር እና ማዳበሪያ በማሰራጨት፣ የተሻሻሉ የእንስሳ ዝርያዎችን በማዳቀል፣ እየሰራ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 25 የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትመህርት ማሰልጠኛ ኮሌጆችና 8 ሺህ 489 የአርሶ አደሮች ማሰልጠኛ ማዕከላት ተገንብተው የውስጥ ቁሳቁስ ተሟልቶላቸው ወደ ስራ ገብተዋል፡፡

ከ25ቱ የግብርና ማሰልጠኛ ኮሌጆች 100 ሺህ የሚጠጉ የልማት ጣቢያ ሰራተኞችን በማሰልጠን ማሰማራት ተችሏል፡፡ ይህም አርሶ አደሩን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ በማድረግ በኩል በ1983 ዓ.ም ከነበሩት 3 ሺህ የልማት ጣቢያ ሠራተኞች አንፃር ዕድገቱ ምን ያህል እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህም በእያንዳንዱ ቀበሌ በተለያዩ የሙያ መስኮች ሶስት ባለሙያዎችን ለመመደብ ግብ ተጥሎ ይህንን ለማሳካት በየክልሉ ሰፊ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

የግብርናው ዘርፍ በምርምር እንዲታገዝ ለማድረግም በተለያዩ ክልሎች 62 የሚደርሱ የግብርና ምርምር ማዕከላትን ለማቋቋም ተችሏል። ተቋማቱን ለማጠናከርም በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር የሰለጠኑ 1ሺህ 253 ተመራማሪዎች ተመድበዋል።

የግብርና መር ኢኮኖሚያችንን ይበልጥ ለማሳደግ ከፍተኛ መጠን ያለውን መሬት በመስኖ ለማልማት በርካታ ስራዎች በመሠራት ላይ ናቸው። ቀደም ሲል ለበርካታ ዓመታት መሬቱን በመስኖ ለማልማት የሚያስችል ውጤታማ ፖሊሲም ስላልነበረ እስከ 1993 ዓ.ም ድረስ በአጠቃላይ በአገሪቱ የለማው መሬት እጅግ በጣም ጥቂት ነበር።

ከ1993 ዓ.ም በኋላ ሁሉን አቀፍና የተቀናጀ የውሃ ኃብት ፖሊሲ በመውጣቱ ለግብርና መር ኢኮኖሚያችን የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት በሚያስችል መልኩ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። የመስኖ ልማትን በማስፋፋት በአርሶ አደር ደረጃ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ትርፍ አምርቶ

ለገበያና ለኢንዱስትሪው ጥሬ ዕቃነት ማቅረብና የውጭ ምንዛሪን ማስገኘት በሚያስችል ስልት ተቃኝቶ ሰፋፊ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተግባራዊ ተደርገዋል።

የመስኖ ልማት ከፍተኛ ገንዘብ ምቹ የመሬት አጠቃቀምና በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል የሚጠይቅ ነው። ከአቅም ጋር የተገናዘበና ከልማት ስልታችን ጋር የተጣጣመ አስተማማኝና ዘለቄታዊ የመስኖ ልማት ዝርዝር ጥናትና ዲዛይን ስራና ግንባታዎች በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች እየተካሄዱ ይገኛሉ። ከ1996 ዓ.ም በፊት መካከለኛና ከፍተኛ የመስኖ ልማት ሊካሄድባቸው የሚችሉ ግድቦች ሁለት ብቻ ተገንብተው ነበር። እነሱም የአልዌሮ ግድብ (ጋምቤላ) እና የጎዴ (ሶማሌ) የመስኖ ግድብ ናቸው። ግድቦቹ በአጠቃላይ 12 ሺህ ሄክታር መሬት ለመስኖ የማልማት አቅም ነበራቸው።

ከ1996 ዓ.ም በኋላ በርካታ የመስኖ ግድቦች ግንባታዎች ተካሂደዋል። በአማራ ክልል ቆጋ ግድብና መስኖ ልማት 7ሺህ 104 ሄክታር፣ ርብ ግድብና_መስኖ ልማት 14 ሺህ ሄክታር፣ መገጭ ግድብና መስኖ ልማት 17 ሺህ ሄክታር፣ በአፋር ክልል ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት 60 ሺህ ሄክታር፣ ከሰም ግድብና መስኖ ልማት 20 ሺህ ሄክታር፣

በኦሮሚያ ክልል አርጆ ግድብና መስኖ ልማት 50 ሺህ ሄክታር ፣ ዝዋይ መስኖ ልማት 6 ሺህ ሄክታርና በደቡብና ኦሮሚያ ክልል መካከል ጊዳቦ ግድብና መስኖ ልማት 11 ሺህ ሄክታር መሬት የማልማት አቅም ያላቸው ግድቦች የግንባታ ሥራ በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አማካይነት እየተከናወነ ይገኛል።

በአሁኑ ወቅት የአብዛኞቹ የመስኖ ግድቦች ግንባታ ተጠናቆ ሥራ የጀመሩ ሲሆን ቀሪዎቹ ግንባታቸው እየተፋጠነ በመሆኑ ከሶስት ዓመት በኋላ ሙሉ በሙሉ ይጠናቀቃሉ ተብሎ ይጠበቃል።

በአገራችን ከ1996 ዓ.ም በፊት የተካሄደ የመስኖ ልማት ዝርዝር ጥናት ያልነበረ ሲሆን ከ1996 ዓ.ም በኋላ ማለትም ከ1996-2002 ዓ.ም 457 ሺህ 287 ሄክታር መሬት ለመስኖ ልማት ተጠንቷል።

የመስኖ ልማት በየአካባቢው መስፋፋቱ ድህነትን ለማጥፋት ከሚኖረው አስተዋጽኦ በተጨማሪ የዝናብ ወቅትን ብቻ ጠብቆ ሲጠቀም የነበረውን ህዝብ ወደላቀ ምርታማነት ደረጃ እንዲሸጋገር የሚረዳው ነው። የምርታማነት ደረጃውን ይበልጥ ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት በ2004/2005 የምርት ዘመን በግብርና ሚኒስቴር አማካኝነት 910 ሺህ 50 ኩንታል ምርጥ ዘር ለማሰራጨት ተሰብስቦ ተዘጋጅቷል። ከዚህ ውስጥ 416 ሺህ 334 ኩንታል የበቆሎ ዘር፣ ቀሪው 493ሺህ 716 ኩንታል ምርጥ ዘር ደግሞ ሌሎች ድቃይ ያልሆኑ የብርዕ፣ የጥራጥሬና የቅባት እህሎች መሆናቸውን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ካሰራጨው መረጃ መረዳት ተችሏል።

የሃገሪቱን የግብርና ምርታማነት በሔክታር በአማካይ 18 ኩንታል ለማድረስ በሚደረገው ርብርብ በምርት ዘመኑ 253 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል።

በማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭት በኩልም በምርት ዘመኑ ለማቅረብ ታቅዶ የነበረው 950 ሺህ ቶን ማዳበሪያ ውስጥ 888 ሺህ ቶኑ ከውጭ በማስመጣት የሚሸፍን ነው። ከዚህ ውስጥ 762 ሺህ 188 ቶን የሚሆነው ማዳበሪያ ወደሃገር ውስጥ ገብቶ ለየክልሉ ተሰራጭቷል።

ሌላው የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን ህይወት ለመለወጥና ምርታማ ለማድረግ ሲሰራበት የነበረው የገጠር አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ተጠቃሽ ነው። ፕሮጀክቱ በግብርናው ዘርፍ ለውጥ ለማስገኘቱም የአርሶ አደሩ፣ የአርብቶ አደሩና የግብርና ባለሙያው አኗኗር እየተለወጠ መምጣቱ ምስክር ነው።

በካናዳና በስዊድን መንግስታት ድጋፍ ባለፉት አምስት ዓመታት በመላው አገሪቱ ሲከናውን የነበረው ፕሮጀክት መጠናቀቁን አስመልክቶ በመልካሳ የግብርና ምርምር ተቋም በተካሄደ የመዝጊያ መርሐ ግብር ላይ የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ወንድይራድ ማንደፍሮ እንደገለፁት የገጠር አቅም ግንባታ ፕሮጀክት በሳይንሳዊ አስተሳሰብ እንዲቃኝና ዘመናዊ የገጠር አቅም ግንባታ ፕሮጀክት በሳይንሳዊ አስተሳሰብ እንዲቃኝና ዘመናዊ እንዲሆን በማድረግ ፕሮጀክቱ ተጠቃሽ ለውጥ ማስገኘቱን ጠቁመው፣ በተለይ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ በገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን በአነስተኛ ማሳ በማምረት በገበያ ዋጋ እንዲሸጥ ማድረግ መቻሉን አብራርተዋል።

የገጠር አቅም ግንባታ ፕሮጀክት በግብርና እና ቴክኒክ ሙያ ማሰልጠኛ በኤክስቴሽን መርሐ ግብር እንዲሁም በግብርና ምርምር ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ እንዲመጣ እገዛ አድርጓል። በተለይ ገበያ ተኮር የሆኑ ምርቶችን በአነስተኛ ማሳ ላይ ለማምረት የተደረገው ጥረት የገጠር አቅም ግንባታ ስራ ወጤታማ እንደነበር የሚያስረዳ ነው። ፕሮጀክቱ ውጤታማ ስለነበር መንግስት በራሱ ወጪ በጀት መድቦ ለማስቀጠል እየተዘጋጀ ነው።

ግብርናው ውጤታማ እንዲሆንና አርሶ አደሩ ጤናማ የግብይት ስርዓት እንዲመቻችለት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካበረከቱት ድርጅቶች አንዱም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ነው። የምርት ገበያ በዘንድሮው የበጀት ዓመት 601 ሺህ ቶን ግብይት አከናውኗል። ግብይቱ ካለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር ከ23 በመቶ ብልጫ አለው።

የምርት ገበያው 329 አባላትና 10 ሺህ 416 ደንበኞች ያሉት ሲሆን የመሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራትና የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየኖችን ተሳትፎ በእጥፍ በማሳደግ ከ111 ወደ 193 ማድረስ ችሏል።

ለአዲሱ በጀት ዓመትም የምርት ገበያው የኤሌክትሮኒክስ ንግድ ለመጀመር ማቀዱ፣ በምግብ ሰብሎች ገበያ ተሳታፊ የሚሆንበት አሰራር መንደፉ፣ ከአርሶ አደሮችና ከህብረት ስራ ማህበራት ጋር የሚገናኝባቸውን ፕሮግራሞች የመቅረጽ ስራዎች እንደሚያከናውን መጠበቁ የበለጠ ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል የሚያሳይ ነው።

በአጠቃላይ መንግስት በቀየሰው ምቹ ፖሊሲ አማካይነት የሃገራችን ኢኮኖሚ ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ባለ ሁለት አሃዝ ዕድገት እያስመዘገበ መጥቷል። በመሆኑም ዕድገቱን ለማስቀጠል አርሶ አደሩ ከአቅሙ ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ የግብርና ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ ማድረግ  ይገባል።